**የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር**
(ኢ.ብአግ)

**Ethiopian National United Front**
**(ENUF)**

# የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር
## ጋዜጣዊ መግለጫ

**ግንቦት ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.**

**የኢትዮጵያ ሕዝብ ኣንቅሮ የተፋው የሻዕቢያዊ/ወያኔ አምባገነን አገዛዝ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ግንቦት ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. እትም የሚከተለውን መሠረት የሌለው የሀሰት ውንጀላና ፕሮፓጋንዳ በመጠቀም በኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር (ኢ.ብአግ) እና አባላት ላይ ክስ ሰንዝሯል። የአሜሪካን ናሳ (NASA - National Aeronautic and Space Administration) የጠፍር መንኰራኲር ፈጣሪና አብራሪ የነበረው ገናናው የኢትዮጵያ አርበኛ ሳይንቲስት እንጅነር ዶ/ር ቅጣው እጅጉ ከስድስት ዓመት በፊት መሥርቶ እስከ ዕለተ እረፍቱ ሲመራ የቆየው የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር (ኢ.ብአግ) ዛሬም የመሥራቹን ራዕይ በመከተልና የድርጅቱን አርማ በማንገብ በኢትዮጵያ ውስጥና በዓለም ዙሪያ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲመሠረት ከፍተኛ ተጋድሎ በማድረግ ላይ ይገኛል።**

**ትላንትም ዛሬም በጦር መሣሪያ ኃይል የኢትዮጵያን ሕዝብ በትረ-መንግሥት ጨብጦ ሕዝብ ለመረጣቸው ተወካዮች አላስረክብም ያለው ጉልበተኛ ወያኔ በድርጅታችን ላይ በሃሰትና በቅጥፈት የሰነዘረው ውንጀናላ ክስ ከዚህ እንደሚከተለው ይነበባል።**

### የወያኔ ክስ

3በመንግሥት ላይ የትጥቅ አመጽ ለማራመድ ተንቀሳቅሰዋል በተባሉ ተጠርጣሪዎች ላይ ክስ ተመሠረተ

አዲስ አበባ - የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ የትጥቅ አመጽ ለማራመድ ተንቀሳቅሰዋል ባላቸው 55 ሰዎች ላይ ትናንት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ መሠረተ፡፡

ዓቃቤ ሕግ ክሱን የመሠረተው የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የፖለቲካ ፐርቲ እና መሥራች ድርጅቶች አባላትና ደጋፊዎች በመሆን ሲንቀሳቀሱ ከቆዩ በኋላ የግንቦት 97 ምርጫን ምክንያት በማድረግ በሕገ መንግሥት በተቋቋመው የኢትዮጵያ መንግሥት ላይ የትጥቅ አመጽ ለማራመድ ተንቀሳቅሰዋል ባላቸው ግለሰቦች ላይ ነው፡፡

ዓቃቤ ሕግ እንዳመለከተው፤ ተከሳሾቹ ራሱን የኢትዮጵያ [ሕዝብ] ብሔራዊ አንድነት ግንባር ወይም የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ አንድነት አርበኞች ግንባር በሚል ሕገ ወጥ ድርጅት ሥር ሕዝባዊ ማዕበል፣ በትጥቅ ትግል የሚደገፍ አዲሱ ቅንጅት፣ ሕቡዕ እንቅስቃሴ በሚሉና በሌሎች ተቀጥላ ስያሜዎች ይንቀሳቀሱ ነበር፡፡

**P. O. Box 21387, Washington, DC 20009 • U.S.A. •**
**Telephone (202) 785-1618**
**www.enufforethiopia.org**

ከተከሳሾቹ መካከልም 37ቱ በዕለቱ በሁለተኛ ወንጀል ችሎት ቀርበው ዓቃቤ ሕግ የመሠረተባቸው ክስና የማስረጃ ዝርዝር እንዲደርሳቸው ተደርጓል::

የግንቦት 97 ዓ.ም የአገራዊ ምርጫን ውጤት መታወቅን ተከትሎ ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የፖለቲካ ድርጅት መሥራች አባል ድርጅቶች ሕገ መንግሥቱንና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል የማፍረስ ሙከራ ወንጀል በሕቡዕ እና በትጥቅ በተደገፈ አመጽ ለመቀጠል አቅደው ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ በሚች ቅጣው እጅጉ መሪነት ከኢትዮጵያ ውጭ ቡድኑ መመሥረቱን የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ ካቀረበው ክስ ለመረዳት ተችሏል::

የሕቡዕ ድርጅቱ የአመራር አባላት ነን በሚሉ ነዋሪነታቸው ከኢትዮጵያ ውጭ አሜሪካ እና ጀርመን በሆኑት መሥፍን ኃይሌ እና ለጊዜው ትክክለኛ ስማቸው እና የአባታቸው ስም በውል ባልተረጋገጠው አበበ፣ እንደሻው፣ ለምለም፣ ሣምሶን፣ ፋሲካ፣ አለሙ በተባሉት ግለሰቦችና ወኪሎቻቸው አማካይነት ተመልምለው ለተደራጁት የአሁኑ ተከሳሾች ቀጥታ የስልክ ግንኙነት ያደርጉ እንደነበር ተመልክቷል::

ተከሳሾቹ ከአገር ውስጥና ከአገር ውጭ በሚሰጣቸው አመራር፣ ገንዘብና ተንቀሳቃሽ -ሞባይል? ስልክ እየታገዙ ከነሐሴ ወር 1998 ዓ.ም ጀምሮ እጃቸው እስከተያዘበት ታኅሣሥ ወር 1999 ዓ.ም በአዲስ አበባ፣ በደቡብና በአማራ ክልሎች የተለያዩ ከተሞች ተደራጅተው በመንቀሳቀስ ላይ እንደነበሩ ዓቃቤ ሕግ ለፍርድ ቤቱ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ አብራርቷል::

በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ዓቃቤ ሕግ በግለሰቦቹ ላይ የመሠረተውን ክስና የማስረጃ ዝርዝር በዕለቱ እንዲደርሳቸው ተደርጓል:: ለተከሳሾቹ ግንቦት 30 ቀን 1999 ዓ.ም የክስ ቻርጁ የሚነበብላቸው መሆኑን ችሎቱ በመግለጽ እስከ ቀነ ቀጠሮው ባለው ጊዜ ተጠርጣሪዎቹ በማረሚያ ቤት እንዲቆዩ ትዕዛዝ ሰጥቷል::4

---

**ከዚህ በላይ የተነበበው የወያኔ መሠረተ ቢስ ውንጀላና ክስ የኢትዮጵያ ሕዝብ በየአለበት በአልሞት ባይ ተጋዳይነት በወያኔ አገዛዝ ላይ የሚሰነዝረውን የአመፅ ማዕበል ዘወትር በማሰብ፣ በመፍራትና በስጋት ተወጥሮ ወያኔ የረጨው ፕሮፖጋንዳ ከመሆን አያልፍም።**

---

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር የተመሠረተው በነሐሴ ወር ፲፱፻፺፫ ዓ.ም. ሲሆን፣ በአሜሪካን መንግሥት ሕግ መሠረት በኅዳር ወር ፲፱፻፺፭ ዓ.ም. ተመዝግቦና እውቅና አግኝቶ የሚንቀሳቀስ ሕጋዊ ድርጅት ነው።

ኢ.ብአግ በመጽሔት፣ በድረገጽ፣ በጋዜጣዊ መግለጫዎች፣ በድርጅቱ 3የሕዝብ ድምጽ ሬድዮ4፣ በሕዝባዊ ስብሰባዎችና በሲዲ (CD) የድርጅቱን ዓላማና የፖለቲካ ስልት በጠራ መልኩ

**P. O. Box 21387, Washington, DC 20009 • U.S.A. •**
**Telephone (202) 785-1618**
**www.enufforethiopia.org**

ለሕዝብ አስተላልፏል። እንጅነር ዶ/ር ቅጣው እጅጉ ከዚህ ዓለም በሞት ከመለየታቸው በፊት በጥቅምት ወር ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. አትላንታ፣ ጆርጅያ፣ ሰሜን አሜሪካ ያደረጉት ንግግር ተቀድቶና CD ላይ ተቀርፆ በኢትዮጵያና በቀረው ዓለም ዙሪያ በመሰራጨቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ የኢ.ብአግ ዓላማ እና ግብ ምን እንደሆነ በሚገባ ተረድቷል። በመሆኑም ማንኛውም የወያኔ ውንጀላና የስም ማጥፋት ዘመቻ ድርጅታችንን ለአንዲት ደቂቃ እንኳን ሲያዘናጋ ፈጽሞ አይችልም። እነዚህን መረጃዎች ከኢ.ብአግ ድረገጽ ላይ http://www.enufforethiopia.org ማግኘት ይቻላል።

በመሆኑም የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር ግብ ዓላማና ፕሮግራም ግልጽ ሆኖ ሳለ፣ ድርጅቱ የሚያካሂደው የትግል ስልት ሁለገብ ነው። ይህም ማለት በፀሎት፣ በሰላማዊ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ፣ በዲፕሎማቲክ ግንኙነት፣ በሙያና በማሕበረሰብ ትብብር፣ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወያኔ በሰላማዊ በሕዝብ ላይ የጦር መሣሪያ ሲመዝና ሲያጠቃ የአልሞት ባይ ተጋዳይነት የመከላከል እርምጃዎችን ያጠቃልላል።

የወያኔን የሃሰት ውንጀላ በተመለከተ፣ የኢ.ብአግ አመራርና አባላት በሙሉ ውንጀላው ሃሰት መሆኑን ለሕዝብ እያሳወቁ፣ የወያኔ አምባገነን ገዢዎች የተከሳሾቹን ስም እንኳን አጣርተው ሳይለዩ፣ 3ስማቸው እና የአባታቸው ስም በውል ያልተረጋገጠው ተጠርጣሪዎች4 በማለት ሰላማዊ ዜጎች ታፍነው፣ ወያኔ በቆራጥ የኢትዮጵያ አርበኞች ላይ ሲፈፅም የቆየው ሰቆቃና እጣ ፈንታ ደርሷቸው፣ ቁጥራቸው በገሀድ የታወቀው ሃምሳ አምስት የሚሆኑ ዜጎች ታስረውና ተሰቃይተው ያለ ፍርድ በመንገላታት ላይ ይገኛሉ።

በክሱ እንደተጠቀሰው ከሆነ፣ መስፍን ኃይሌና 3እንደሻው4 ተብለው የተሰየሙት ተከሳሾች ግን ምናልባትም በነዚህ ስሞች የሚታወቁ የድርጅታችን አባላትና የኢ.ብአግ ማዕከላዊ አመራር ኮሚቴ አባላት ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ግምት አለን። የኢ.ብአግ አባላት አቶ መንፍን ኃይሌና አቶ እንደሻው በፍፁም የወያኔን 3ሕገ መንግሥቱንና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል የማፍረስ ሙከራ4 አድርገውም አያውቁም። አላደረጉምም።

ኢ.ብአግ፣ ቅንጅት በወርሃ ግንቦት ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. በቆራጥ ሰላማዊ ትግል ተንቀሳቅሶ፣ በሕዝብ ተደግፎ ያበሰረውን የዴሞክራሲ ጮራ እያደነቀ፣ የድርጅቱ አመራር አባላትም የሕዝብን ድምጽ አናሰርቅም በማለት ያደረጉትን የጀብድ ሰላማዊ ትግል እያከበረ፣ የሕዝብን የዴሞክራሲ ፍላጎትና እምነት ለማዳፈን የወንጀለኛው የሻዕቢያ/ወያኔ አመራር አባላት መለስ ዜናዊ፣ አባይ ፀሓዬ፣ ስንሃት ነጋ፣ በረከት ስምዖንና ስዩም መስፍንና ተላላኪዎች የፈፀሙትን ሕገ ወጥ የሰብአዊ መብት ገፈፋና ግድያ አጥብቆ ይቃወማል። ኢ.ብአግ፣ የቅንጅት አመራርና አባላት ከቀሩት የኢትዮጵያ የተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶች ጋር በመቀራረብና በመወያየት የሚያደርጉትን ጥረት እየደገፈ፣ ባለፈው ዓመት የተመሰረተውን "ትብብር ለአንድነትና ለዴሞክራሲ" መልካም ጅምር መሆኑን አምኖ ድጋፉን ማበርከቱ ይታወሳል። አሁንም ድጋፉን በድጋሜ ያበስራል። በተረፈ ወያኔ ኢ.ብአግንና ስመ ጥሩውን ቅንጅት

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር
(ኢ.ብአግ)

Ethiopian National United Front
(ENUF)

ከሌላ አልባሌ ድርጅት ጋር አምታትቶና አዛምዶ ለመወንጀል ያደረገውን ሙከራ ድርጅታችን አጥብቆ ያወግዛል።

ኮሎኔል አሥራት ቦጋለ የተሰኘ ግለሰብ ቀደም ሲል በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት የዩኒቨርሲቲ ዘበኞች አዛዥ በመሆን በሰላይነት ተማሪዎችን ሲያስገድል የቆየና፣ በደርግ የግፍ አገዛዝ ዘመን በባለሥልጣንነት ለሠራዊቱ እንዲያቀብል በአደራ የተሰጠውን ስልቅ፣ ትጥቅና ደመወዝ በሔሊኮፕተር ጠልፎ ወደ ጅቡቲ ከገባ በኃላ፣ ወደ ፓሪስ ዘልቆ ለፈረንሳይ መንግሥት በሰላይነት ተግባር ተሰልፎ ባለፉት ፴ ዓመታት ሲያገለግልና 3የኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድነት ንቅናቄ4 የተሰኘ የአርበኞች ቡድን መሪ ነኝ በማለት ሕዝብ ለስደተኞች መረዳጃ የሰበሰበውን ገንዘብ ተረክቦ በየበረሃው ለሚጉላላው ወገን ሳያደርስ፣ ለግል ጥቅም እያዋለ አውሮፓ ተንደላቆ በመኖር ላይ ይገኛል።

ይህ ግለሰብ የድርጅታችንን አርማ፣ ተመሳሳይ ስምና መዛግብት በመጠቀም ሕጋዊነት በሌለው ተግባር ተሠማርቶ የኢ.ብአግን እና የሳይንቲስት ቅጣው እጅጉን ስም ለማጉደፍ ሙከራ ቢያደርግም፣ ከድርጅታችን ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንደሌለው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያውቀው እናስገነዝባለን። ኮሎኔሉ አውሮፓ መስርቻለሁ ያለውን የግለሰብ ንቅናቄ ወደጎን በመተው ወደ አትላንታ፣ ጆርጂያ፣ አሜሪካ አቅንቶ፣ ከአንድና ሁለት የማይበልጡ ተባባሪዎችን ይዞ ለመንቀሳቀስ መሞከሩ የተንኮል ሂደት መሆኑን ሕዝብ ሊገምት ይችላል። ምናልባትም ኮሎኔል አሥራት በከፍተኛ ሚስጢር የተያዘውን የኢ.ብአግ አባላት ስም ዝርዝር አግኝቶ ለወያኔ ሽጦ ይሆናል የሚል ግምት አለን።

በመጨረሻም ወያኔ በኢ.ብአግና በአባላቱ ላይ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ መክፈቱን በአሜሪካን ድምጽ ሬድዮ ግንቦት ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. በተላለፈው ዜና ከሰማን በኋላ፣ ሁለት በዝግጅቱ ክፍል የታወቁ ጋዜጠኞችን በስልክና በኢንተርኔት አግኝተን በሬድዮ ዘጋቢያቸው ከአዲስ አበባ ስለተላለፈው የሀሰት የወያኔ ውንጀላና ክስ ምላሽ እንድንሰጥ እድል እንዲሰጠን በተደጋጋሚ ብንጠይቅም እድሉ ስለተነፈገን የተሰማንን ቅሬታ ሕዝብ እንዲያውቅልን እናሳስባለን።

የመጨረሻው ድል የኢትዮጵያ ሕዝብ ይሆናል።
የአትዮጵያ ሕዝብ የ፫ኛ ሺ ምዕተ ዓመት በድል ዋዜማ ያከብራል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ግንባር
ማዕከላዊ አመራር ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ
ዋሽንግተን ዲሲ